የሰ/መ/ቁ. 79212

ጥቅምት 19 ቀን 2005 ዓ.ም

.

ዳኞች፡- ተሻገር ገ/ስላሴ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አዳነ ንጉሴ

መኰንን ገ/ሕይወት

አመልካች፡- ሮያል ከረሜላ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ አቶ መድህን መሐሪ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ፀሐይ ብርሀኑ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የተጠሪ የሥራ ስንብት በአሠሪው (በአመልካች) አነሣሽነት የተፈፀመ ነው ወይስ በተጠሪ (በሠራተኛዋ) ጠያቂነት የተፈፀመ ነው የሚለውን ጭብጥ የሚመለከት ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከህግ ውጭ ከሥራ ያሰናበተኝ በመሆኑ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የተለየዩ ክፍያዎች እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበችው ክስ ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ሥራቸውን በፈቃዳቸው የለቀቁት ከቅርብ አለቃቸው ጋር ባለመግባባታቸው ነው፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ (ከሣሽ) ወደ ሥራቸው እንድትመለስ በቃልና በጽሑፍ የጠየቋት ቢሆንም ከሣሽ (ተጠሪ) ወደሥራዋ ለመመለስ ፈቃደኛ አልሆነችም፣፣ ከሣሽ (ተጠሪ)ን ከሥራ ለማሰናበት ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ የሥራ ውላቸው አልተቋረጠም፡፡ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ ፈቃድ ነው የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሥራ ውሉ የተቋረጠው በአሠሪው ነው ወይስ በሠራተኛው ተነሣሽነትና ፈቃድ የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቷል፡፡ ተጠሪ ሥራውን የለቀቅሁት የቅርብ አለቃዬ ሥራውን እንድለቅና እንድሄድ ስላዘዙኝ ነው በማለት ጭብጥ አስይዘው ምስክሮች አስምተዋል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ከሥራ ውጪ ካላት በኃላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የቀረበችበት ደመወዝ

ተከፍሏት ከቅርብ አለቃዋ ጋር የተፈጠረው ችግር ተስተካክሎ ሥራውን ለመቀጠል የምትችል መሆኑን ተጠይቃ ተጠሪ እንቢተኛ መሆኗን አመልካች አስረድቷል፡፡

ስለዚህ ተጠሪን ከሥራ የማስናበት ሥልጣን የሌለው ሰው ከሥራ ውጪ በማለት ተናግሮኛል በማለት ወደ ሥራ እንድትመለስ ብትጠየቅ እንቢተኛ በመሆኗ የሥራ ውሉ የተቋረጠ በመሆኑ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በተጠሪ ፈቃድ (አነሣሽነት) ነው በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 520 (አምስት መቶ ሃያ ብር) የዓመት እረፍት ፈቃድ በገንዘብ ተቀይሮ ብር 190.67 (አንድ መቶ ዘጠና ብር ከስልሣ ሰባት ሣንቲም) እና የዘጠኝ ቀን ደመወዝ ብር 48 (አርባ ስምንት ብር) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርባለች፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይግባኝ ባይ በቅርብ አለቃቸው ከሥራ እንዲወጡ መደረጉ ተረጋግጧል፡፡ የይግባኝ ባይ የቅርብ አለቃ ሠራተኛ የማሰናበት ሥልጣን የሌላቸው መሆኑና ይግባኝ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ተጠይቀው ወደ ሥራ ለመመለስ አለመስማማታቸው ስንብቱን ህጋዊ አያደርገውም፡፡ ስለዚህ አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በህገ ወጥ መንገድ በመሆኑ፣ የመጀመሪያ ደረጃው ፍርድ ቤት ከወሰናቸው ክፍያዎች በተጨማሪ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ መልስ ሰጭ ለይግባኝ ባይ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 25 ቀን 2004 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ የቅርብ አለቃዋ ሥራዋን እንድታቋርጥ ከተናገራት በኋላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ስራዋን እንድትቀጥል የነገራትና እንቢተኛ ሆና ከሥራ ገበታዋ የቀረች መሆኑ እንደተረጋገጠ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በውሣኔው አስፍሯል፡፡ ይህ ፍሬ ጉዳይ ህግ ወጥ ስንብትን ያሣያል በማለት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረታዊ ዓላማ ያልተከተለና የህግ መሠረት የሌለው ነው በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በቅርብ አለቃዬ ተዘልፌና ሞራሌ ተነክቶ ነው፡፡ ሥራ አስኪያጁም ይህንን የቅርብ አለቃዬን ተግባር ደግፈዋል፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው መባሉ ተገቢ ነው በማለት ሐምሌ 30 ቀን 2004 ዓ.ም መልስ ሰጥታለች፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሰናበታት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ የማስጠንቀቂያና የካሣ ክፍያ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርመረናል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ከስራ እንድትወጣ የተናገራት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተጠሪ የቅርብ አለቃ ተጠሪን ሥራ ለቅቃ እንድትወጣ ከተናገራት በኋላ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪን ቢሮ ድረስ በማስጠራት በቅርብ አለቃዋ የተሰጠው ትእዛዝ ተገቢ እንዳልሆነ፣ የቀረችበት ቀን ደመወዝ እንደሚከፈላትና ወደ ሥራዋ እንድትመለስ ጠይቋት ተጠሪ ወደ ሥራ ለመመለስ ፈቃደኛ ያልሆነች መሆኑን የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪን ሥራ ለቅቃ እንድትሄድ የተናገራት የተጠሪ የቅርብ አለቃ በድርጅቱ ያለው ኃላፊነት በሥራ መሪነት የሚያስመድበውና፤ በሥራ መሪነቱ የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነትም ሠራተኛ ለማሰናበት የሚያስችለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2(ሐ) በአዋጅ ቁጥር 494/98 እንደተሻሻለው ተጠሪ አላስረዳችም፡፡ በሌላ በኩል የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የቅርብ አለቃ ስራዋን እንድትለቅ መወሰኑ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ ወደ ሥራዋ እንድትመለስ ተጠሪን ጠይቀዋት ተጠሪ እንቢተኛ በመሆኗ የሥራ ውሉ የተቋረጠ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

አንድ ሠራተኛ ከሥራ ለማሰናበት ስልጣንና ኃላፊነት የሌለው የቅርብ አለቃው ከሥራ ለቅቆ እንዲሄድ ስለተናገረው ብቻ፣ አሠሪው የሥራ ውሉን አቋርጦታል ብሎ ለመደምደም አይቻልም፡፡ ሠራተኛው የሥራ ውሌ ተቋርጧል ከማለቱ በፊት የቅርብ አለቃው በሥራ ያለውን ሠራተኛ፣ ከመምራትና ከመቆጣጠር ባለፈ በሠራተኛው ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ለመውሰድና ያለውን ሥልጣን በተለይም ከሥራ የማስናበት ሥልጣን ያለው መሆኑን ወይም አለመሆኑን የማወቅና የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ ተጠሪ የቅርብ ኃላፊዋ ሥራ ለቅቃ እንድትወጣ ቢናገራትም የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የቅርብ አለቃዋ እሷን ከሥራ የማሰናበት ስልጣን እንደሌለው ገልፀው ወደ ሥራ እንድትመለስ ጠይቀዋል፡፡

ይህ ከሆነ አመልካች የሥራ ውል ለማቋረጥና ተጠሪን ከሥራ ለማስናበት ሥልጣንና ኃላፊነት ባለው የሥራ መሪ በኩል የሥራ ውልን አቋርጧል ብሎ ለመደምደም የሚያስችል የህግ መሠረት የለም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ በቅርብ አለቃዋ ሥራ እንድትለቅ የተናገራት መሆኑ ብቻ የሥራ ስንብቱን ህገ ወጥ ያደርገዋል፡፡ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ወደ ሥራ እንድትመለስ መጠየቁ ህገ ወጥ ስንብቱን ህጋዊ አያደርገውም በማለት የሰጠውን የህግ ትርጉም የአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ዮ